# ስለ ምርጫ የተሳሳተ መረጃ ማግኘት

ስለ ምርጫው ሂደት፣ ስለ ድምጽ ሰጪዎች መብቶች፣ ወይም በድምጽ መስጫ ካርድ ላይ ስላለው ጉዳይ የተሳሳተን መረጃን የማሰራጨት ተግባር በድምጽ መስጫ ደኅንነት ላይ ጥብቅ የሆነ ስጋት ነው። እነዚህ ጥረቶች - የውጪ ሀገር ሰዎች፣ ነዋሪው፣ ወገንተኛ፣ ወይም በቀላሉ ተንኮለኛ ቢኖኑም - የእኛን የምርጫ ሂደት ላይ ታማኝነት እንደሌለው ለማሳየት የተጠነሰሱ እና ጤናማ የሆነውን የዲሞክራሲን መንገድ የሚያጠፉ ናቸው።

## የተሳሳተን መረጃ መጋፈጥ

እውነትን በማወቅ ጎጂ የሆነውን የተሳሳተውን መረጃ መጋፈጥ ምርጫችን ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እና የሰዎችን ትክክለኛውን ፈቃዳቸውን የሚገልጸውን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የዲሞክራሲ ሂደታችንን ለማቆየትም በጣም አስፈላጊ ነው።

በጣም በርካታ መጠን ያላቸው መረጃዎች ስለሚገኙ፣ ከምን ጊዜውም በላይ የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀማችን በጥልቀት ማሰብ እና ከተለያያዩ ምንጮች የሚመጡትን ተፎካካሪ የሆኑትን በርካታ መልእክቶችን መለየት በጣም አስፈላጊ ነው።

በታሪኩም ወይም በአባባሉ ላይ እውነተኛ መሆኑ ላይ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ተአማንነት ያላቸው፣ ወገንተኛ ያልሆኑ የተረጋገጡ መረጃዎችን በእነዚህ በሚከተለው ድኅረገጾች ላይ ያገኛሉ፡-

- **Michigan.gov/SOSFactCheck –** ስለሚሽንጋን (Michigan) ምርጫዎች ትክክለኛውን መረጃ ይሰጣል
- **Snopes.com –** የተሳሳተ መረጃን፣ የማጭበርበሪያ ትወራዎችን፣ ማጭበርበር እና ተጨማሪ የሆኑ ነገሮች ለመመረመር እና እርባና ቢስ መሆናቸውን ለማወቅ
- **FactCheck.org –** የፖለቲካ ንግግር፣ ማስታወቂያ፣ ክርክሮችን፣ ቃለመጠይቆች፣ እና የህትመት ውጤቶችን እውነታ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ
- **PolitiFact –** በፖለቲከኞች የተደረጉ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ

## የራስዎን ድርሻ ይወጡ!

ምርጫውን የሚያካሄዱት ባለሥልጣናት  ስለ ምርጫው የተሳሳተ መረጃን እንደሚለዩት እና ሕግን መሰረት ባደረገ መልኩ ትክክለኛውን መረጃ በፍጥነት እንደሚሰጡት ሁሉ፣ ድምጽ ሰጪዎችም በንቃት ታአማኝት ያላቸውን የመረጃ ምንጮችን የመፈለግ እና ፍሬ ያለውን እና ቅንነት ያላቸውን ውይይቶችን ለማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው።

በሚሽጋን (Michigan) ስለ ድምጽ መስጫው ወይም ስለ ምርጫዎቹ የሚያሳስቱ ወይም ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎችን ካዩ፣ እባክዎን ሪፖርት ያድርጉት — እና ከተቻለ ምስሉንም አካተው — ወደ **Misinformation@Michigan.gov** ያላኩ።

የሚቺጋን ስቴት መምሪያ ክፍል (Michigan Department of State)

# ድምጽ ለመስጠት እንዴት መመዝገብ ይቻላል

በሚቺጋን (Michigan) ውስጥ ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ፣ በምርጫው ቀን አካቶ በርካታ መንገዶች አሉ፤ ነገር ግን በተቻለ ፍጥነት መመዝገብ ግን ምርጥ መንገድ ነው።

## እርስዎ ብቁ ኖዎት?

በሚቺንጋን (Michigan) ውስጥ ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ ብቁ ለመሆን፣ በሚችጋን (Michigan) ውስጥ ነዋሪ ሆነው ከምርጫው ቀን ቀደም ብሎ ቢያንስ ለ 30 ቀናት ያህል በከተማዎ ወይም በመንደርዎ መኖር፣ የዩናይትድ ስቴት ዜጋ መሆን፣ በአሁን ጊዜ በማረሚያ ቤት ወይም በእስር ቤት የማይገኙ፣ እና በምርጫው ቀን ቢያንስ 18 ዓመት ሊሆንዎት ይገባል።

## ለመመዝገብ የሚኖሩ አማራጮች

ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ ወይም የድምጽ ሰጪነት ምዝገባዎን ለማዘመን ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

- በኢንተርኔት ቀጥታ መሰመር ላይ – ይህን ይጎብኙ Michigan.gov/vote እና Register to vote online የሚለውን ይጫኑ።
- በፖስታ መልእክት – በድምጽ ሰጪ የፖስታ መላኪያ መመዝገቢያ ቅጽን በ Michigan.gov/VoterRegForm ላይ ያውርዱ ወይም ቅጹ በፖስታ እንዲላክልዎት ይጠይቁ።
- በስቴት ጸሐፊ ቅርንጫፍ ቢሮ– ለመንጃ ፈቃድ ወይም ለስቴት መታወቂያ ዝውውር የስቴት ጸሐፊ ቅርንጫፍ ቢሮን እየጎበኙ ከሆነ፣ መምረጥ ካልፈለጉ በስተቀር ወዲያውኑ ድምጽ ለመስጠት ይመዘገባሉ። ለሌላ ዓይነት ዝውውር እርስዎ እዚያው የሚገኙ ከሆነ፣ የድምጽ መስጫ መመዝገቢያ ቅጹን ሊያስረክቡ ይችላሉ።
- በእርስዎ ወረዳ፣ ከተማ ወይም መንደር የዋና ጸሐፊው ቢሮ – በአከባቢዎ በሚገኘው ዋና ጸሐፊዎ ጋር ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ ከመረጡ፣ ፎቶ ያለው መታወቂያ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። በስቴት የሕዝባዊ ድጋፍ ቢሮ ማለትም የጤና መምሪያ ክፍል እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ጋር ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ ይችላሉ።

## የቀነ ገደብ ቀኖች

ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ የቀነ ገደቡ እና በሚመጣው ምርጫ ላይ ድምጽ ለመስጠት ለመቻል፣ ወደ ከተማዎ ወይም የመንደርዎ የዋና ጸሐፊ ጋር በአካል ቀርበው ሳይሆን በማንኛውም በሌላ መንገድ ተመዝግበው ከሆነ ከምርጫው ቀን ከ15 ቀን በፊት ነው።

በምርጫው ቀን ድምጽ ለመስጠት እስከ 8 p.m. ድረስ በእርስዎ ከተማ ወይም መንደር ውስጥ በዋና ጸሐፊዎ ቢሮ የነዋሪነትዎ በማረጋገጥ መመዝገብ እና ከዚያም እዚያው እያሉ ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

**የሚቺጋን ስቴት መምሪያ ክፍል (Michigan Department of State)**

# የቀሪ ድምጽ እንዴት መስጠት ይቻላል

ምንም ዓይነት ሰበብ ወይም ምክንያት አያስፈልግዎትም – በሚቺጋን (Michigan) ውስጥ ሁሉም ደምጽ ሰጪ ተመዝጋቢዎች የቀሪ ደምጽ መስጫ ካርድን በመጠቀም አሁን ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

## ለቀሪው የድምጽ መስጫ ካርድን ለመጠየቅ በርካታ መንገዶች አሉ፡-

- ወደ Michigan.gov/Vote ይሂዱ እና በኢንተርኔት ቀጥታ መሰመር ላይ ቅጹን ይሙሉት።
- ማመልከቻውን ያውርዱ እና በፖስታ አድርገው ወይም በአካል ወደ ከተማዎ ወይም ወደ መንደርዎ ዋና ጸሐፊ በመሄድ ይመልሱ።
- ወደ ከተማዎ ወይም የመንደሪዎ ዋናው ጸሐፊዎ ጋር ይደውሉ እና ማመልከቻው በፖስታ እንዲላክልዎ ይጠይቁ።
- በአካል ወደ ከተማዎ ወይም መንደርዎ ዋና ጸሐፊ ቢሮ ይሂዱ።

በኢንተርኔት ቀጥታ መሰመር እና በፖስታ በኩል ለቀሪ የድምጽ መስጫ መጠይቆች በከተማዎ ወይም በመንደርዎ ዋና ጸሐፊ ከምርጫው ቀን በፊት ባለው ዓርብ ላይ ከ 5 p.m. በፊት ተቀባይነት ማግኘት አለበት።

በአሁኑ አድራሻዎ አስቀድሞም ተመዝግበው ከሆነ፣ በዋና ጸሐፊው ቢሮ ከምርጫው ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት በማንኛውም ጊዜ እስከ 4 p.m. ድረስ በአካል ቀርበው የቀሪ የደምጽ መስጫ ካርድን መጠየቅ ይችላሉ።

የቀሪ የደምጽ መስጫ ላይ ድምጽ ለመስጠት ካቀዱ፣ በታቻለ መጠን ቀደም ብለው የቀሪ የድምጽ መስጫ ካርድን ይጠይቁ። ማመልከቻዎች ከምርጫው በፊት እስከ 75 ቀናት ድረስ መቅረብ ይችላል።

## የእርስዎን የቀሪ የደምጽ መስጫ ካርድዎን ማስረከብ፡-

- የድምጽ መስጫ ካርድዎ ላይ ምልክት ያድርጉ እና ተመላሽ የሚሆነው ፖስታ ላይ መፈረምዎን እና ማሸግዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
- የተሟላው የቀሪ ድምጽ መስጫ ካርድዎ በከተማዎ ወይም በመንደርዎ ዋና ጸሐፊ በምርጫው ቀን በ 8 p.m. ላይ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።
- በፖስታ ወይም በእጅ በመላክ የደምጽ መስጫ ካርድዎን በዋና ጸሐፊዎ ቢሮ ወይም በመልእክት ማስቀመጫ ሳጥናቸው ውስጥ ማስረከብ ይችላሉ።
- በምርጫው ቀን በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የእርስዎን የድምጽ መስጫ ካርድዎን ከመለሱ፣ በእጅ ¬በእርስዎ ዋና ጸሐፊ ቢሮ ወይም በመልእክት መላኪያ ሳጥን ውስጥ በፖስታ ቢላክ ሊከሰት የሚችለው መዘግየትን ለማስቀረት ካርድዎን ያስረክቡ።

## የሚቺጋን ስቴት መምሪያ ክፍል (Michigan Department of State)

# በምርጫው ቀን ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ

የሚቺጋን (Michigan) ሕግ በተመሳሳይ ቀን የድምጽ መስጫው ቀን መመዝገብን ይፈቅዳል። ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ እና በድምጽ መስጫው ቀን በእርስዎ ከተማ ወይም በመንደርዎ ዋና ጸሐፊ ቢሮ ውስጥ እስከ 8 p.m. ድረስ በማንኛውም ጊዜ በአካል ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

የብቁነት እና የነዋሪነት ማረጋገጫዎን ማምጣት ይኖርብዎታል፦

### የብቁነት ማረጋገጫ፦

ድምጽ ለመስጠት ለመመዝገብ ብቁ ለመሆን እርስዎ መሆን ያለብዎት፦

- የሚቺጋን (Michigan) ነዋሪ (በሚመዘገቡበት ጊዜ) እና ቢያንስ ለ 30 ቀናት (ድምጽ በሚሰጡበት ጊዜ) በከተማዎ ወይም በመንደርዎ ነዋሪ መሆን
- የአሜሪካ ዜጋ
- ቢያንስ 18 ዓመት ዕድሜ (ድምጽ በሚሰጡበት ጊዜ)
- በአሁኑ ጊዜ በእስር ቤት ወይም በወህኒ ቤት ውስጥ ቅጣት ላይ ካልሆኑ

### የነዋሪነት ማረጋገጫ፦

የሚኖሩበት ቦታ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማሳየት አለብዎት። ሰነዶቹ የእርስዎን ስም እና የአሁኑን አድራሻ መያዝ አለበት። የሰነዶችን ኮፒን በዲጂታል ማሳየት ይችላሉ። ተቀባይነት ያላቸው ሰነ¬ዶች የሚያካትቱት፦

- የሚቺጋን (Michigan) የመንጃ ፈቃድ ወይም የስቴት መታወቂያ
- በአሁኑ ጊዜ የሚጠቀሙበትን የፍጆታ ደረሰኝ
- የባንክ ሂሳብ ማረጋገጫ
- ፔይቼክ ወይም የመንግሥት ቼክ
- ሌላ የመንግሥት ሰነድ

# በአካል ድምጽ መስጠት

ተመዝግበው ከሆነ፣ በከተማዎ ወይም በመንደርዎ ዋና ጸሐፊ ቢሮ ውስጥ የቀሪ ድምጽ መስጫ ካርድን በመጠቀም ቀደም ብለው ድምጽ መስጠት ይችላሉ። የሆነ ሆኖ፣ የድምጽ መስጫው ቀን ከሆነ፣ እና የድምጽ መስጫ ካርድ ከሌልዎት፣ በአከባቢዎ የድምጽ መስጫ ቦታ ላይ ድምጽ መስጠት ብቻ ይችላሉ።

የደምጽ መስጫ ሳጥኑ በአከባቢው ከ7 a.m. እስከ 8 p.m. ባለው የአከባቢው ሰዓት የሚከፈት ሲሆን በ8 p.m. ሰዓት ላይ በሰልፍ ላይ እስከሆኑ ድረስ ድምጽ ለመስጠት መብት አልዎት።

## የድምጽ መስጫ ቦታ ማግኘት

ይህን ድኅረገጽ Michigan.gov/Vote በመጎብኘት በቀላሉ የድምጽ መስጫ ቦታን ወይም የእርስዎን ከተማ ወይም መንደር ዋና ጸሐፊ መረጃን ማግኘት ይችላሉ።

### ምን ይጠበቃል፡

ወደ ድምጽ መስጫ ቦታዎ በሚደርሱበት ጊዜ፣ ፎቶ ያለው  መታወቂያ እንዲያሳዩ ይጠየቃሉ።  ተቀባይነት ያለው መታወቂያ የሚያካትታቸው:

- የመንጃ ፈቃድ ወይም በሚቺጋን (Michigan) ወይም በሌላ ስቴት የተሰጠ የስቴት መታወቂያ
- በፌዴራል፣ በስቴት ወይም በወታደራዊ መንግሥት - የተሰጠ የፎቶ መለያ
- የዩኤስ ፓስፖርት
- ከሁለተኛ ደረጃ ወይም ዕውቅና ያላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪ መሆኑን የሚገልጽ ፎቶ ያለው መታወቂያ
- ዘሩ ማን መሆኑን የሚገልጽ ፎቶ ያለው መታወቂያ

ፎቶ ያለው መታወቂያ ባይኖርዎትም፣ ነገር ግን ድምጽ መስጠት ይችላሉ።  የድምጽ ቆጠራ ሠራተኛ ድምጽ ከመስጠትዎ በፊት መታወቂያ የሌልዎት መሆኑን የሚገልጸውን ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠይቆታል።

ከዚያም እርስዎ ንቁ የሆኑ የድምጽ ሰጪ መመዝገቢያ ዝርዝር ላይ ይፈርሙ እና የድምጽ መስጫ ካርዱ እና እርስዎም የሰጡትን ድምጽ ምስጢራዊነቱን ለመጠበቅ እንዲሸፍኑ እጅጌ ይሰጥዎታል።

የድምጽ መስጫ ካርድዎ ላይ ምልክት ለማድረግ ወደ ድንኳኑ ውስጥ ከገቡ በኋላ፣ የድምጽ መስጫ ካርዱን በእጅጌ ውስጥ አድርገው ይመልሳሉ።

አንዴ የእርስዎን የድምጽ መስጫ ካርድዎን ወደ ድምጽ መስጫው ውስጥ ከከተቱ፣ በሕጋዊነት ድምጽዎን ሰጥተዋል ማለት ነው።
እኔ መርጫለሁ" የሚለውን የሚለጠፍ ነገር ካለ መውሰድዎን እርግጠኛ ይሁኑ።